ከ 1945 -2008 ዓ.ም.

## የአቶ ዘለአዓለም ብርሃኑ (ድሉ)

## አጭር የሕይወት ታሪክ

አቶ ዘለዓለም ብርሃኑ ከአባቱ ከአቶ ብርሃኑ ሞገስ እና ከእናቱ ከወ/ሮ ዓይኔ ፀጋዬ አንደ ኢትዮጲያ አቆጣጠር መጋቢት ወር 1945 ዓ.ም. በጎጃም ክ/ሀገር በባህር ዳር አውራጃ በዘጌ ከተማ ኡራ ኪዳነምህረት ተብሎ የሚጠራው ገዳም ተወለደ።

እድሜው ለትምህርት እንደደረሰ በዚሁ ከተማ ትምህርት ጀምሮ ብዙም ሳይቆይ ወደ ባህር ዳር ከተማ በመሔድ የአንደኛና የሁለተኛ መለስተኛ ትምህርቱን አጠናቆ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በመከታተል ላይ አንደነበር በአገራችን የ1966 ዓ.ም. ለውጥ ወይም ኣብዮት መጣ። በዚህን ጊዜ ዘለዓለም ብርሃኑ በኣገራችን ታላቁን ታሪካዊ ምዕራፍ የያዘውን ወደ ስልሳ ሺህ ወጣቶች የተሳተፉበትን የዕድገት በህብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ የተሳተፈ ተካፋይ ነበር።

ሁሉም እንደሚያውቀው በዚህ ዘመቻ የተሳተፈ ሁሉ

የፖለቲካ ሀሁ የተቆጠረበት
የፖለቲካ ፀበል የተቀመሰበት
የፖለቲካ ፀበል የተረጨበት
በአጠቃላይ የፖለቲካ ምንነት የተቀሰመበት ዘመቻ ነበር።

ዘለዓለም ቀልጣፋ ደፋር ተናጋሪና ለነገሮች ሁሉ ቀድሞ ደራሽ በመሆኑ በዘመቻ በነበረበት ግዜ ሁሉ ዘማች ወደየመጣበት ሲመለስ ዘለዓለም ከአሥራሦስት ጓደኞቹ ጋር ከዘመቻ ጣቢያው ታሥሮ ቀረ። ከሦስት ወር በኋላ ከእሥር ቤት ተፈቶ ወደ ባህር ዳር መጣ።

ከዚያ በኋላ በ1969 ዓ.ም. ከሁሉም ቀድሞ ከጓደኞቹ ጋር ወደ አሲንባ አመራ፤ ከነሙሉጌታ መንገሻ ጋር። ሙሉጌታ መንገሻ በአለፈው ዓመት በግንቦት ወር በሲያትል፣ ዋሽንግተን የሞተው አንጋፋ የኢ.ህአፓ ታጋይ ነበር።

ከዚያም ትግሉ የጠየቀውን ሁሉ መስዋት እየከፈለ ትግሉን ቀጠለ። ከተራ ተጋዳይነት እስከ ሃይል መሪ የደረሰ ሲሆን በትግሉ ውስጥ እንደነበረ በጦርነት ላይ ቆሰለ። የመቁሰሉን አደጋ እንዲያገግም በህክምና ላይ በነበረበት ወቅት እጁ ቃታ መከፈትና ምላጭ መሳብ ይችላል ወደ ጦርነቱ ልመለስ እያለ ሃኪሞችን ያስቸግር እንደነበር እስከአሁን ድረስ ይነገርለት ነበር።

ከዚያም በትግሉ መርዘምና በትግሉ ውስጥ በተፈጠረው ችግር እንደ ሌሎቹ ሁሉ በ1981 ዓ.ም. በዚህ አገር አቆጣጠር ከባለቤቱ ከወ/ሮ አበባ ተፈሪ ጋር ወደ አሜሪካ መጣ። ከዚያም ከባለቤቱ ጋር ሳምሶን ዘላለምን ወልደው ኑሮዋቸውን ቀጠሉ።

ዘላለም በቨርጂኒያ እየኖረ በአንድ የግል ትምህርት ቤት በመግባት የሚገባውን እውቀት ከተማረ በኋላ በሙያው በመስማራት ኑሮውን ሲቀጥል በደረሰበት ህመም ለረጅም ግዜ በህክምና ላይ ቢቆይም ህመሙ እየበረታ በመሄዱ በሞት ሁላችንንም ተለየን።

**አምላክ ለዘመድ አዝማድና ለጓደኞቹ መፅናናቱን ይስጥልን!!**

*ከኢትዮጵያ፣ ከአሜሪካ የተለያዩ ከተሞች በመደወልና በመምጣት*
*ላጽናናችሁንና የሃዘናችን ተካፋይ ለሆናችሁ በሙሉ ምስጋናችን የላቀ ነው፡፡*

ቤተሰቡና ጓዶቹ

ከቅድስቷ ቦታ ጣና ከደሴቱ ዘጌ ተወልደህ
ተቆላምጠህ ነበር አንተማ የአደግህ
የትግል ማዕበል ሁሉን ሲአለጨንቀው
ዘላዓለም ነበረ ዋኝቶ የዘለቀው።

ከሂሳቡ ሁሉ መቀነስ ተማርነ
መስብሰቡን ሳይሆን መበተን ወደድነ
እንደወጣን ቀረን መችም አልታደልነ።

ከእንግዲህ ጣና ዳር ዛሬም ይለቀስ
ፎካሪው አለቅ ለበሰ ቀሚስ።

ህብረወርቅ የቄስ ልጅ የተባረከች
ከወንድሟ ጋራ ዘመቻ ሄደች።

ገበያ ወጥች መልካም ገበየሁ
እራሴን ወዳዱ ድሉን አስቀደምሁ።

ፀሐይዋ ስትሞቅ ነው የሚረግፍ ጤዛ
ስንቱ ጀግና አለቀ እንዲህ እንደዋዛ።

የሰው አገር አፈር አይበላኝም ብሎ
ለቀሪዎች ሰጠ አካላቱን ክፍሎ።

ሳንጨርሰው ቀረን ጉዞአችን ረዝሞ
መቅበር ብቻ ሆኑ ዘንድሮና ከርሞ።

ያንን መከራ አልፍህ የአሁኑ ነው መልካም
አፈር ከለበሱ መዋረድ አይነካም።

መዘዙን ስንፈትሽ የእለፍህበትን
ከጀግንነት በቀር አታውቅም ፍርሃትን።

ተንጠራርተህ ተኛ ምቹ ነው ትራሱ ወደ መደላደሉ
እንግዲህ አይሰጉም የሚፈሩህ ሁሉ።



**አቶ ዘለአዓለም ብርሃኑ (ድሉ)**



**ከ 1945 -2008 ዓ.ም.**